# ቅዱስ ፍቅር መጽሀፍ

## ክፍል ሁለት



# ፍቅርሲዝም ሀይማኖት

አዘጋጅ እና አቅራቢ :  ነብይ ደምሳሽ በሀይ

554

## የዩንቨርስ  አፈጣጠር በፍቅርሲዝም

በመጀመርያ አምላክ ዩንቨርስን በሙሉ በ 1 ደቂቃ ፈጠረ  ጸሀይ መላው ፕላኔቶች  ሁሉ አሳምሮና አስውቦ ለሰው የአስተሳሰብ አድማስን ና አምላክን ለማመስገን ና ታላቅነቱን ለማስረዳት አስውቦና እጁጉን አስፍቶና አብዝቶ መላውን ዩንቨርስ ምድርን ጨምሮ ፈጠረ ።

555

በመቀጠል  በ2ኛው ደቂቃ በምድርላይ አየር ንፋስ ውሃ እጽዋትንና እንስሳትን ናነፍሳትን ባጠቃላይ መላው ፍጥረታትን   ለሰው ልጅ  ለአስተሳሰቡም  ለምግብነትም ሆነ ለመነፈሳዊ ህይወት እንዲመች አድርጎ ሁሉንም አሳምሮ ና ድንቅና ውብ አድርጎ  በየደረጃውና በየዘርፉ በምድር ላይ ያለውን ሁሉ አሳምሮ ና አስውቦ   ና ድንቅ አድርጎ ፈጠረ ።

556

## በ3ኛው ደቂቃ ና የመጨረሸው የፍቅር አምላክ እግዚአብሄር  6 ሰዎችንና 3 ሰይጣኖችን  ጋር እኩል ፈጠረ

ሁሉም እኩሉ ተፈጠሩ ሰዎቹም ሆኑ ሰይጣኖቹም በ 6 አመታቸው በተመሳሳይ ደቂቃና ሰከንድ አኩል እድገት እንዲኖራቸውም አድርጎ ሰራቸው ሰዋቹም ሆኑ   ሰይጣኖቹም  የሰውን ክፉ ሀሳብ ተከትለው  ሰይጣኖቹም እንዲጉዋዙና እንዲራመዱ ሰውንም ሆም ብለው እንዲያሳስቱ  ና አብረውም ከሰው ጋር እንዲየድጉ በክፍ ሀሳብ ሰውን እንዲያጎለብቱ ሰይጣኖችም ከፍተኛ ሀይልና ተሰጣቸው  በማሳሳትም ከሀሳብም ተነስተው ተግባርና ድርጊት ብሎም ሀሳብን ም ሆነ ተግባርንም ጭምር መግዛትና ከማሰቃየት እስከሞት ብሎም ሲኦል ድረስ ይዞ የመሄድ ከፍተኛ ስልጣንና መብትም የፍቅር አምላክ ራሱ ሰጣቸውም።ሰይጣኖቹንም በ 3 ከፈላቸው

557

## ሳኮም

ሀሳብን የሚገዛ ሰይጣን ሲሆን ምንግዜም የምናስበውንና የማንመኘውን መጥፎ ሀሳብ እንዲሆንና መንፈስቅዱሰ እንዳይቀርበን መከላከልና በመጥሮ ሀሳብ እኛን መጥመድ ሲሆን ስራው ይህም ሰይጣን አብሮን ከሀሳባችን ጋር ስለሚያድግ  በጊዜ ካላውቅንበት እጅግ በጣም ከባድና አብሮን የሚያድግ በመሆኑ መላው ሀሳባችንን በመቆጣጠር ሰላምና ደስታ በማሳጣት አብሮን ይኖራል።

558

## ካሱር

ይህ ሰይጣን ደግሞ ተግባራችንን በመጥፎና ስሜታዊ አሉታዊ እንዲሆን  እንድንተገብር በማድረግ መላው ስራችን ያልተባረከ ለቁጭትና ንዴት  ለጸጸት ሰላምና እርካታ ለማጣት እንዲኖረንና እንዳንደሰት ያደርገናል ከሱር ከ ሳኮም

የመጣውን ትእዛዝ አምላክን ሳንፈራ ወደመጥፎ ተግባር እንድንፈጽም ና እንድንተገብር ያስገድደናል በማወቅም ባለማወቅም በይሉኝታም በቸልተኝነትም በእንዝላልነትም በመሰላቸትም ጥቅም ፍላጎ በጥላቻ በማማረር አምላክን ተስፋበማጣት /ተስፋበመቁረጥ የሰውንበመመኘት በቅናቻ በጥላቻ በህልህ በብልጠት በማይምነትና ባለማቀቅ ባለማስተዋል በመሳሰሉት ጨለምተኛ አመለካከትና አስተሳሰብ በመነሳት ሳኮም ወደ ተግባር ሳኩት እንድንፈጽም ያደርጉናል እናም ካላስተዋልን እየበዛም ሲመጣ መቆጣጠር ወደማንችለው ካሱም /ሀያሉ ሰይጣን እንወድቃለን።

559

## ካሱም

ካሱም የሚባለው ሰይጣን እጂግ ከባድና ሀይለኛ የመዳን መፍትሄው የጠበበ ደረጃ ስንደርስና ለከፍተኛ ስህተትና ሞት በኛም ሆነ በሌሎች ላይ እንዲፈጸም የሚያደርግ በመጨረሻም ገሎን በምድርም አሰቃይቶን ወደ ሲኦል ይዞን የሚገባ ትልቁ ስልጠን የተሰጥው ሰይጣንነው።

ይህሰይጣን ከሌሎቹ ሰይጣኖች የሚለየው በምድርም ሆነ ከምድርም በዋላ ሰውን በማሰቃየት ከፍተኛ ስልጣንና መብት የፍቅር አምላክ እግዚአብሄር ራሱ ነው የሰጠው

ለፈጣሪ እኛ በፍጹም መገዛት ሳንችል ስንቀርና አምላክን መታዘዝ አሸፈረኝ ስንል ከብዙ ትግስት በዋላ አምላክ ለዙሀ ሰይጣን አሳልፎ ስትወድቅ ዝም ይላል አምላክ አብዝቶ ብዙ እድል ሰቶ ስትቀልድና ስትዳፈር ስህተት ስታበዛ ካሱም ያገኝሀል እባክህ ወንድሜ ህህቴ አስተውሉ የፍቅር አምላክ ከዚ ጉድ ያድናችሁ።

560

## ፍጥረት

## መላውን ፕላኔቶች

## በምድር ላይ የመጡ ነብያቶች

ምድር ስትፈጠር ጀምሮ ፈጣሪን ከሰው እንደዚሁም ስለአምላክ መኖር ሰዎች የሚያውቁበት መንገድ በነብይ አምካኝነት ነው ታድያ ለዚህም ምድር ስትፈጠር ጀምሮ በዚህ ምድር ላይ 150 ነብያቶች መተዋል በ 7 ሚሊየን አመታት ውስጥ ማለት ነው

561

## የመጀመርያው ነብይ

## ሶሎ

በጣም ጎበዝና ጀግና ነበር አምላክም በጣም ስለሚወደው ከስድስቱ ሰዎች ውስጥ አምላክም ይህን ክብር ሰጠው ።ሶሎም ማነው የፈጠረን እያለ ይጨነቅ ነበር ብዙውን ግዜውን በማሰብ ያሰልፍ ነበር ታድያ አንድ ቀን የፍቅር አምላክ እግዚአብሄር ሁሉንም በህልም ገለጸለትናም ነብይ አደረገው ከዚያም ለ 3 እምታት በሰጠው ህግ የበዙትን

ህዝቦች ሲያስተምር ወደ ቀና ሲመልስ አምላክን በህጉ አጽንቶ አቆይቶዋል ሁሉተኛውም ነብይ ከአጎ ዝርያ የተፈጠረው ጥቆር ነብይ ስሙም ሁል ነበር በጣም ትልቅ ስራ በመስራቱ ሰዎች በዚያን ግዜም ከነበሩበት ባእድ አምልኮ አውጥቶዋቸዋል ።በ3ኛው ነብይ ከዛውከጥቁር ህዝብ የመጣ ነው ስሙም ምስሮ ይባላል የማህበረስቡን የጥላቻ አስተሳሰብ መቅረፍ ችሎዋል ማህበረሰቡ እርስ በእርስ ያለው አስተሳሰብና ያለመግባባትን ወደምግባባት አምቶዋል ቀናና ጥሩ አሳቢ ማህበረስብ ተፈጥሮዋል።4ኛውነብይ ሻንጋ የተባለነው የህ ደግሞ እግዚአብሄርን መፍራትን አሳውቆዋል።5ኛው ነብይ ቢሳ 6ኛ ተዋ የማስተዋል ነብይ 7ኛ ቶናስ /ቀና መንገድ/8ኛ ታስካ የእንድነትና የፍቅር ነብይ 9ኛው ጁታን እውነትን በማህበረቡ ላይ አስተምሮዋል 10 ኛ ው ነብይ ክሪክስ የብልሀትንና አምላክን የመታዘዝን ና የመፍራትን አስተምሮዋል እንዲ እያለ በፊት ብዙም ሰዎች ስላልነበሩም ነብያቶች ይመጡ የነበሩት ከ 20 ሺ እስከ 50 ሺ አመታት ድረስ ነብይ አይመጣም ነበር አሁን ከቅርብ ማለትም ከ 30 ሺ አመት ወደዚህ ነብይ በጣም ሰዋችም እየበዙ ሲመጡ ስህተታቸውም ችጎሮቻቸውም እየበዛ ሲመጣ የፍቅር አምላክ እግዚአብሄር ነብይ በጣም ቶሎ ቶሎ መላክ ጀመረ።

562

ከ 10 ሹ አመት ወደዚ የመጡት ነብያቶች በትክክል

- 144ኛ ነብይ ቶማ ሬቻ /መንጻትንና መለምለምን አምላክን መታረቅን/
- 145ኛ ነብይኛ ህና ሂንዱይዚም /ፍቅርና ሰላምን ያመጣ
- 146ኛ ነብይ ሞስ ጁዲዝም / እምነትንና ነሳነትን ያሳየ/
- 147ኛ ነብይ ኮንፊሲየስ ኮንፈሲሺም/ጸባይንና ነጻነትህ ማምጣት/
- 148ኛ ነብይ ጉተማ ቡዳ ቡዲዝም እውቀትንና ብቃትን ጥበብን ተሰቶታል /ቡዲዚም/

149ኛ ነብይ እየሱስ /ክርስቲያን/የጣዎት አምልኮን ለማስቀረትና በመንፈስ ለማጥመቅ የመጣ ፣ የማዳንንና የመፈወስን ጥበብ የተሰጠው

563

ማርያም ድንግል አልነበረችም ግን ከዮሴፍ ጋር በነበራት የፍቅር ግንኙነት ድንግል ሆና በ 1 ግዜ ስህተት እየሱስን አረገዘች ሳታስበው ሰለነበረ በጣም አዝና ሳለች ገብሪኤል መቶ በህልሟ ነብይ ትወልጃለሽ ስሙንም ጆሽዋ በይው አላት ብሎዋት ከነበረችበት መከፋት አጽናናት ዮሴፍም የእየሱስም አባትም ነው የማርያምም በወቅቱ የአይን ጉዋደኛዋ ነበር ።

እየሱስም ማርያም ከወለደችው በዋላም አሳደገችው ከአደገም በዋላ አምላክም በመንፈስ መልአክቶፈችን ልኮላት አስተማረው በመጨረሽም ለነብይነት ብቁ አደረገው ና ነብይነቱንም ማከናወን ጀመረ በመጨረሻም ብዙ ካስተማረ በዋላ እየስስንም ተነኮልበሚሰራው ተአምር ማሰብ ሲጀምሩ አምላክ ከዚህ በዋላ ወደሌላ አገር ሂድና እዛው ቆይ ነብይነትህን በዚህአገር እርቀ ሂድ ጠላት በዝቶብሀልና ብሎት ወደ ሳውዲአረቢያ በመሄድ እዛው አግብቶና ሁለት ሴቶች ልጆች ወልደ ሃዊ ና ታዊ ሙያም የእንጨት ባለሙያ ነበረ በር ፣ጠረጴዛ ወንበር በመስራት ታዋቂም

ባለሙያ ሆነ  እንደዚሁም ሚስቱም ብዙ የቤት እንስሳ በማርባት የበኩሉዋን ታግዘው ነበር እየሱሰም 74 አመት ሲሆነው ሞተ።

564

- 150 ነብዩ መሀመድ

የፍቅር አምላክም በእየሱስ ሲያመልኩ እግዛብሄር ተቆጥቶ ነብዩ መሀመድን በማስነሳት ቁርአንን በገብርኤል አማካኝነት ሰቶት ስሙም አምላክ/እግዚአ ብሄር  ራሱ አላህ ብሎ እንዲጠራ አደረገ እስልምናንም ተፈጠረ አምላከም ልጠፋ የነበረችውንም አለም በነብዩ መሀመድ አማካኝነት ታደጋት።

እስልምናን ያመጣው  ጎበዝና ታላቅ ነብይ  ነው በዚህም አማካኝነት ረጅም አመት ስራው ሳይቀየጥና ሳይበረዝ ቆይቶለታል። ምንም ሆነ ምንም ከጊዜ ብዛት ሰይጣን የጠፈጠረውን አይማኖት ይቆጣጠረዋልና ስለዚህም የአምላክ ክብር ስለሚርቅ አለምም ልጠፋ ስትል አዲስ ነብይ በመምጣት አለም ትድናለችና ወደዛ ው አዲስ ሀይማኖት መሄዲ በተሸለ  መባረክ  መዳን ና ታላቅ እድል  ማግኘት ነው።

565

- 151ኛ ነብይ ደምሳሽ

ከረጅም አመት በዋላ ደግሞ አምላክ ከሁሉም ሀይማኖቶች ራቀ ማህበረሰቡ በተለዪ መልኩ ወደራሳቸው ማንንት ብቻ ማሰብና ሌሎችን መርሳት ጀመሩ እጅጉን ለስሜትና ለመጥፎ ሀሳብ ተገዢም በመሆናቸው አማካኝነት እግዚአብሄር /አላህ  ፍቅርሲዝም ሀይማኖት እንዲፈጠር አደረጉ ።ስ ሙንም የፍቅር አምላክ እግዚአብሄር/እግዚአብሄር  ተብሎ እንዲጠራ ፈለገ በዚህምልጠፋ የነበረችውን አለም ዳነች።

566

-152 ነብይ ከደቡብ አፍሪካ ይመጣል ከ1800 አመት በዋላ  ፍቅርሲዝንም ሀይማኖት ከ1500አመት በዋላ ሰዎች እየቀያየጡና ሀሳባቸውም እየተከፈለ በመምጣቱም ምክንያቱም አለምም  በድጋሚ በሌላ ነብይ አምላክ በማስነሳት ትድናለች።

567

151 ነብያቶች ሲመጡ  151 ሀይማኖትና የአምላክ ስም ተፈጥረዋል አምላክ አንድ ነው አንድ አምላክ ራሱ ነው ይህን ሁሉ የፈጠረው አውቆና ሆም ብል በሌላው ላይ ስሙ ሲረክስ በአዲስ መልኩ በተቀደሰ ነብይ በራሱ በአምላክ ሀሳብ በአዲስ እምነት እንዲፈጠር ይፈልጋልና።አምላክም አዲሱን ሀይማኖት ሀይልና ተሰሚነትን እንዲያገኝ ሰዎችም ሲጸልዩም ሆነ ሲያመሰግኑ ሲጾሙም ሆነ ሲሰግዱ ማንኛውንም የእምነቱን ህግ ሲተገብሩ አምላክ በቅርበት ያዳምጣቸዋልና።

ምክንያቱም አለም ልጠፋ ስትል በነበረው ሀይማኖት ውስጥ ሰዎች ሀይማኖቱን ሲያረክሱት ፈጣሪ አዲስ ነብይ በማስነሳት አለምን በድጋሚ ያድናታል።

ሌላው አምላክ የተለያዩ ሀይማኖቶች መኖራቸውንም ይፈልጋል ።ምክንያቱም በተለየዩ መልኩ የማህበረሰብ አስተሳስብ እሱ በፈቀደው እንዲቆይም ይፈልጋል ስለዚህም በሰዎች አስተሳሰብ ውስጥ ነጻነትና ዲሞክራሲ ናአዳዲስ አስተሳሰኖችና ለችግሮቻችን መፎትሄዎችን እንዲፈጥር ስለሚያስችል ነው።

568

በአለም ላይ አንድ ሀይማኖት ብቻ ቢኖር ለመኖር በጣም አደጋ ነው ሲሳሳቱም የሚያርማቸው የሚመለከታቸው ሌላ አካል አይኖርምና መፈጠር ዘርፈ ብዙ ጥቅም አለው እንጂ ጉዳት የለውም ምክንያቱም መተሳሰብ መከባበር መተዛዘን አለማዳላት አምላክን መፍራት ጥረትና ግረት የተለየ ፍላጎት አዳዲስ አሳብ የመሳሰሉት ባልተፈጠረ ነበር ሰለዚህም ያሉትን በመከባበርና ባለመናቅ በፍቅር ማሸነፍ እንጂ በጉልበት ወይንም በስሜት የለብንም ።ለዚህም ደሞ ቀላሉ መንገድ በማንኛውም መልኩ አምላክን በመፍታት ማሰንና መተግበር ያስፈልጋልና።

569

ግን በመጨረሻው የሚመጣው ሀይማኖት የተባረከ ነው ምንግዜምና በተቻለ መጠን አዲሱን ትክክለኛ ነብይ አውቀን መከተል ያዋጣናል ምክንያቱም አምላክ አሁን የፈቀደው ነውና ።በነበረው ብናመል ይሆናል ግን የአምላክ መንፈስ ከዛ ስለራቀ በጣም አምላክን ለማግኘትና ለማመን በጣም ከባድ እና አስቸጋሪ ብሎም አሰልችና ተስፋ አስቆራጭ ይሆናልና።

570

ሁሉንም ነገር አንድም ሳይሳሳት እግዚአብሄር ፈጥሮታል ስለዚህም እናመስግን ስህተት አትፈልግ ቆሸሻ ጎን ብቻ ማየት ማማረር ነው ።

571

አለም በመጥፎ ስራ ስተቆሸሸ ፈጣሪ አለምን የሚያድናት ሌላ ነብይ ለዛንም የሚሆን ሀሳብ በማምጣት ነው ስለዚህም በየጊዜው የመጡት የተለያዩ ነብያቶች መምጣት እናም አምላክ ራሱ ፈልጎ ነው በተለያዩ ስሞች የተጠራውና ለመጣራትም ለመጸለይም ለመወደስም የሚፈልገው በሀጥያት ባልቆሸሸው እምነትነው ሰለዚህም አሁን ላለነበት ዘመን ህዝቡን ለማዳን ፈቅርሲዝም የመጣው ።

572

እና እባካችሁ መላው የአለም ህዝም የእውነት የምትድኑት ከብዙ መጥፍ ሃሳብና ጭንቀት አምላክ ለናንተ የሚታዘዘው በዚህ አይማኖት ነው ግዜ አታባክኑ ወደፍቅር ቶሎ በፍጥነት ኑ ኑ ኑ

ሰይጣን አሁን ባለንበት አለም አለምን ገዝቶዋታልና መላውን የአለም ህዝብ አሸንፎዋልና ጊዜ አትስጡት ቶሎ በጊዜ ወደፍቅር ኑ

ለአምላክ መታዘዝ ግዴታችሄም ሆነ ውዴታችሁም ነውና የፍቅር አምላክ እየጠበቃችሄ ነው እዚ በጋራ ተሰብስበበን እንድናመልከው ይፈልጋልና

573

ታድያ የፍቅር አምላክ እግዚአብሄር ይህን ሁሉ ሰይጣን የፈጠረው ለምንድን ነው

ምክንያቱም እኛ ራሱ የተፈጠርነው የፍቅር አምላክ እግዚአብሄርን እንድናምን እንጂ  እሱንም ፈርተን እንድንኖር እንድናመልክው በሌላ እንዳንተማመን በሱ ብቻ እምነት እንዲኖረን በፈጣሪም ላይ አብዝተን እንድንምካ ና በፍቅር አምላክ በእግዚአብሄር ብቻ እንድንተማመን ካዘበተረፈ ከሰጋን ከፈራን ከተጨነቅን ከተጠራጠርን ከተጠነቀቅነ ክፉ ክፍውን ካሰብንና ለሰው ካወራንና ራሳንን ካልተቆጣጠርን ራሳችንን በመልካም ልምድ ካላገራን  በቅዱስ ጥሞናና ፍቅር የሀስተሳሰብና የተግባር ልምምዶችን ካልወሰድን በቀላሉ ሰይጣን ይጎዳናልና የምናደርገውንና የምናስበውን አስተውልን የተገራ ማንነት ካልፈጠርን ሳናስበው በብዙ መልክ ብንጸልይም ሆነ ብንሰግድም አንተርፍም ልማዱ በከፍተኛ መልኩ ውስጣችን ሰርጾዋልና  ።

574

ስለዚህም አሁን ላለንበት ችግር የፍቅር አምላክ ን በፍቅርሲዝም መሰረት ብንታዘዝ ና ብንከተል ይሻላችዋል

ካለበለዚያ ግን ዋዋዋ!!!

ስለዙህ ዛሬ ነገ ሳትሉ ቶሎ ወስናችሁ ወደ ፍቅር ኑ

ቅዱሰ ፍቅር ጥሞና/ሃሰብ/  ና ቅዱስ ፍቅር ትምህርተ /ተግባር/

ትምህርት

የፍቅር አምላክ ሰውን በ1 ደቂቃ ፈጠረ እፍግ ብዙ ነገሮችን በ1 ደቂቃ ፈጠረ እሱ የሚሳነው አምላክ ስላልሆነ ሁሉንም በ1 ግዜ ማድረግ አስተካክሎ ሳይሳሳት ቻለ አምላክና ፈጣሪያችን ታላቅ ጌታ ስለሆነ ነው

የፍቅር አምላክ ሁሉንም ይችላልና ለሱ በጣም ትንሽ ነው።

እኛንም እንድንማር የሚፈልገው

**የፍቅር አምላክ እግዚአብሄር**  እንደዚህ አለን በ1 ደቂቃ ውስጥ ፈጠርኩዋችሁ በ 1ደቂቃ ውስጥም ራሳችሁን ከክፍ ሀሳብ  ና ተግባር  ጠብቁ  ካለበለዚያ የሴጣን ንብረት ትሆናላችሁና ዋላችሁ ብሎናልና ።

575

እባካችሁ ሰዎች ስሙ የእውነት ነው አስተውሉ አምላክ የነገረኝን ነው የምነግራችሁ የምታስቡትን ትኩረታችሁን አምላክ ላይ ካደረጋችሁ መንፈስቅድስ ይመራችዋል ካለበለዚያ ግን በካሱም ትያዛላሁ ና ትለከፋላችሁ መውጫችሁም ከባድ ይሆናል።

576

ስለዚህም እኝ  ራሳችንን ለማግራት እንድንችል ቅድስ ፍቅር ጥሞና  ሃሳብን መቆጣጠር አምላክ ላይ ትኩረት በማድረግ ከክፍ ሀሳብ በመራቅ መልካም ና ቀና ሀሳብን የማሰብ ልምምድ ተፈጠረ።

ምንድነው የምናስበው

ምንድነው ያማረን /የምንፈልገው

ስለሰዎች  ያለን ሀሳብ ምን ይመስላል እንወዳቸዋለን ይቅርታ እናደርግላቸዋለን

እየፈራን እየሰጋን እያሰጨነቀን እያሳሰበን እያስደነገ|ጠን ያለ ሀሳብ ምንድነው ለምን

ለምንድነው የምንፈልገውን የማንተገብረው የማንፈጽመው

ለመተግበር ምንያዘን

ሰሜታዊ አሉታዊ ትግበራስ የማናቆመው

በስሜትና በመጥፎ ተግባርስ የምንነዳውአምላክን የማንፈራው

ለምንድን የማናምነው

በሃሳባችን ውስጥ ስለአምላክ ያለን እውቀትና ክህሎት ስለሱ መተማመንማ አለመተማመን ራሳችንን ማጤንና ማሰስ

577

## መፍትሄዎች/እምነትንና የ ምናመጣበት/

ውስጣችን የነበሩትን ክፍ ሀሳቦች ምንግዜም ሳንረሳበመልካም ሀሳብ የመተካትና የማለማመድ ተግባር በየእለቱ ከጸለይን በዋላና በውሎዋችን ውስጥ በሃሳባችን የመተካት ስራ ማባዛት ማላምድ ና  በማስተዋል እያንዳንዱዋን ደቂቃ መዋል  ና ከሀሳብ ወደ ተግባር ማምጣት መለማመድ

578

ለምሳሌ  :ፍራቻ ሲሰማን የምንፈራውን ቦታ ና ሁኔታ በእምነት ካሰብን በዋላ ወደተግባር እዛእምንፈራው ቦታ በመሄድ በአምላክ ላይ ያለንንድፍረት በመተግበር የአምላክን መተማመን መፈጸም።

579

ልክእንደዚሁለ ሁሉ ለተጨነቅንባቸው እምነት ላጣንባቸው ከሀሳብ ወደ ተግቦር የዘለሉ ማንነቶቻችንን ሀሳብን በማቆም እና በመልካም ሀሳብ በመተካት በመቀጠል የተግባር ልምምድ በማድረግ ደካማ የምንላቸውን ማንነቶቻችንን ማላመድና በአምላክ እምነት ውሰጥ የማኖር ልምምድን በማድረግ በሀሳቦቻንና በተግባሮቻችን የሚመጡትን መጥፎ ሀሳቦች ና ተግባሮች ማለትም ሰኮምናሳኮር የማስወጣትና በመንፈስ ቀዱስ ለመታጀብ የሚያስችለንን እምነት እስከምናገኝ ደረስ አጥብቀን ቸል ሳንል የሀሳብና የልምምድ ተምህርቶችን ሳንረሳ በማስተዋለል የፍቅር አምላክን በመፍራት መተግበር።

580

እኛ በአይናችንን  የምናየው  በውስጥ ግንዛቤያችንን እንዲፈጠር ያደርጋል

ማለትም በእይናችንን የምንመለከተው ማንኛውም እይታ ሀሳብ በመሆን ግንዛቤ በውስጣችን እንዲፈጠር ያደርገል በውስጣችን አሁን ያለው ማንኛውም ግንዛቤ የእይታችን ውጤት ነው

አምላክን ባለመፍታት የምናየው በችልተኝነት የምንመለከተው ማንኛውም ሀሳብና እሳቤታ በሙሉ ባለማወቅ ያየናቸው ማለማስተዋል ትኩረታችንን ስሜታዊ ማንነት ላይ አብዝተን ስናተኩር

581

ለምሳሌ ሴት በየመንገዱ ማየት ፣ወሬ ማየት፣ሰዎችንን ማየት ምንአሉኝ እያሉ ራስን መመልከት ራስን መታዘብ፣የሰውንማየት፣መመኘት ፣መቅናት፣መጥላት ማንቋሸሽ ማብጠልጠል  በየሄድንበት በገባንበት የትኛውም ቦታ ሁሉ ዝም ብለን ማየትና ማሰላሰል ይፈጠራል

582

ቅድስ ፍቅር ጥሞና በየትኛውም ቦታ ልምምድ ማድረግ ይኖርብሀል የትም ሄድክ የትም  የትም ገባህ የትም ምንም አደረክ ምንም በመጀመርያ አምላክህን በመፍራት መጉዋዝ  የምታየውን በማስተዋል ና አምላክህን በመፍታት ማየት መጀመር አለብህ ከዛም አስተሳሰብህን በቀላሉ መቆጣጠር በቀላሉ ትችላለህ እና የምትፈልገውን ሀሳብ ሆም ብለህ የምታስበውን ለማወቅ ይረዳሀል ።በየትኘውም ቦታ ሄድክም ምንም አደረክም ምንም ሀሳብክን መቆጣጠር ሰችል ደሞ እይታክን ደግሞ መቆጣጠር ትችላለህ እርስ በእርስ የተያያዙና የተቀናጁና የተሳሰሩ ናቸው ወደሀሳባችን የሚገባውን እይታ ስንቆጣጠር ከሀሳባችን የምናየውየምንፈልገው መሆን ይችላል::

583

ከሀሳባችን የምናየውየምንፈልገው መሆን ይችላል መልካም እይታና ግንዛቤ ና ድርጊት እንዲፈጠር ማድረግ እንችላለን በአምላክ ላይ በመተማመን ላይ ካተኮርን በማስተዋልም ከተገራን

584

የምንፈልገውን ማየት እንችላለን  እይታችን በእምነትና በፍቅር ሲጎለብት

የምንፈልገውን ማየት እንችለለን ግን የምናየውን የምናውቅና  በትምህርት የምናስለምድ ከሆን  ታላቅ አምነትይሆናልና ወይንን እምነት ይፈጠራል ማለት ነው።

585

ህልማችን እውን ይሆናል አምላክን በመፍራት የምናይ ፣የምንሰማ ፣የምንናገር፣የምናዳምጥ ከሆነ በማንኛውም ሁኔታና መልኩ በውስጣችን የምነፈልገው ግንዛቤና እሳቤታ እንዲፈር የምናደርገውን ማወቅአለብን አለበለዚያግን ብኩን እንሆናለን ።

586

እምናየውን የማንቆጣጠር ከሆነ ደግሞ በህየውታችን ውስጥ የማንም ሀሳብ አሉታዊነት ሁሌም በህይወታች ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ በመያዝ እምናደርገውንም ሳናውቅ እምናየውንም ሳናውቅ እምናስበውንም ሳናውቅ የትእነዳለንና ምንእንደምናደርግና እንደምንወስን አናውቅምና የምናየው ሁሌም የሚያበሳጨን ይሆናል ማለት ነው።

587

በውስጣችንን አምላክን አለመፍታት አድጎና ገዝፎ የምናየውንና የምንሰማው መልካም እነዳይሆን የሚያደርገው አስደንጋጭ ወሬ አስቀያሚ ነገሮች በዙርያችን ማየት የቻልነው በመጀመርያ የተመኘነውን ነው የህም አምላክ ተግባራችንን ነው የሚሰማንና የምናየውን አምላክን ባለመፍራት ና ለጊዜያዊ ደስታና ስሜት ፈራቻና ሰጋት ልባችን ውሰጥካለ አዎ ይሂንኑ እንመለከታለን የፈራነው ይደርሳልና ።

588

የፍቅር አምላክን በመፍታት መዋል ማለት የምንሰማውን የምናየውን የምናወራውን የምናዳምጠው ማሰተዋልና በእምነት መድረግ ስንችል መልካም ማዳምጥ መልካምም ማየት መልካምም ነገር መስማት  ማሰብ፤መገንዘብ /ጥሩ ወሬ መስማት ና ማዳመጥእንችላለን የምንችለው እኛበመጀመርያ ጥሩ ስናወራና ስናዳምጥ ስንመለከት ብቻ ነው/ይሄ እምነት እየሆነ በአምላክ ላይም እየተማመንን ም እንድንሄድ ያደርገዋልና ።

589

ስለዚህም አባካችሁ የፍቅር አምላክን እግዚአብሄርን የመፍራት  ማለት በማንኛውም ስሜት አካላችን ምንም ስንፈጽም እያስተዋልንና እያሰብን እናድርገው ስናይ ፣ስንመለከት፣ ስንነካካ ስ፣ናዳምጥ ፣ስናወራ በይበልጥ በየትኛውም ቦታና ሁኔታ ውስጥ ሆነን አምላክን በመፍራት  መዋልና መኖር ማለት የሄ ነው ።

590

የሄኔ አምላክም ላንተ ዘብ ይቆምልሃልና የምትፈልገውን ያሳይሀል አብዝተህ ስትጥር እናእሱንም ስትፈራ አምላክም አብዝቶ ለአንተ ይቆምልሀልና የፈጣሪም መገኘት እንደስራህ  እሱም ካንተ አብዝቶ ይገኛልና በሰው ሳይሆን በፈጣሪ አስተውለህ ተመካ እባካችሁ ሞኝ አትሁኑ አስተውሉ።

591

ይሄ ቅዱስ ፍቅር ጥሞና ከብዙ መጥፎ ሁኔታዋች አምላክህን በመጡመን አሳልፍ አጉል ሱሰ ሆኖብህ  እያሳለፍከው የአለከው ህይወት ቆም ብለህ ተመልከተው  ምንያክል በውስጥህ የተንሰራፋው ጥላቻ ፍራቻ፣ ሰጋት፣ ስሜታዊነት፣በልብህም ሆነ በውስጥህ የምታስበው ና የምትፈጸመው እያደረክ የአለከው አስተሳሰብ ምን እንደሆን አምላክን በመፍታት ላይ የተመሰረተ ማንነት ነው ያለህ ወይንስ አይደለም ምንግዜም በየደቂቃው ራስክን አጢን እናም አዲስ መንገድ ና እድል በስፋት በህይወትህ እንዲመጣ ሀሳብህንና ስሜትህን በመቀየር እድልክን መፍጠርና ማሳመር በእጅህ ነውና።

592

ጥሩ ነገር እንዲገጥምህ መልካም ወሬ መሰማት ከፈለክ  እድለኛ መሆንከፈለክ አንተራሱ በቅድሚያ ጥሩ ሁን ጥሩንአዳምጥለይተህ ሰማ  ቀና ተናገር ቀና ፈጽም አምላክን በመፍታት ሴሜትህክን ተቆጣጠር ከክፍእይታና እሳቤታ ናድርጊትና ውሳኔ ተቆጡብ ከዛም አምላክ ከአንተ ጋር ሰለሚሆን አድል በእጅ ትሆናለችና የፈለከውን ሄሉ የማግኘት ችሎታና ብቃቱ ተአምር ቀላል በአጁጉ ይሆንልሀልና።

593

ይህ ሁሉ በቀላሉ መሆን የቻለበት ምክንያት በዋነኝነት መንፈስአብሮን ስለሚጉዋዝና ስለሚንቀሳቀስ ሀሳባችንን ተከትሎ ስለሚሄድ  በእየአንዳንዳን እሳቤታችንን ስለሚከተል ነው።

594

መንፈስ አይታየንም ሰለዚህ እንቀልዳለን እናፌዛለን እናሾፋለን  እናላግጣለን አምላክን ሳንፈራ ውሎዋችን በሙሉ በግዴለሽነና በሞኝነት በተላላነት ያወቅን መስሎን ብዙ ያጣን መጥፎ መንፈስ የቀረበን በመሆናችን ምክንያት አምላክን ርቆን ሰይጣን አንጎል አድርጎን ህይወታንን በሙሉ በማንፈልገውና ባልፈቀድነው መልኩ እንመራለን ።

ታድያም ውጤቱ የማንፈልገውን ህይወት ይሆናል።

595

**እጅግ በጣም በፍቅርሲዚም የሚወገዝና  የሚከለከል  አምላክ አብዝቶ የሚጠላው ምህረቱ ከባድ የሆነ**

**ተቃራኒ ጾታ ጋብቻና ግነኙነት መፈጠር**

ወንድና ወንድ እንደዚሁም  ሴትና ሴት ግንኙነት አጥያቱ ና ምህረት ለማግኘት በእውነት በጣም ከባድ ነውና ተጠንቀቁ ከዚህ ስራ በጣም ተቆጠቡ ራቁ ቅጣ በምድርም ሆነ በሰማይ ከባድነውና

ከጋብቻ በፊት የሚፈጠር  ግንኙነትና የተለያዩ የግብረስጋ ግነኙነት አስመልክቶ መፈጸም ና የሚሰሩ ፊልሞችን መከታተልና ማየት ማሰብ መመኘት እጅግበጣምና ወደሞት የሚያመራ ስህተትን ያሰከትላል የአምላክ መንፈስ ክፍኛ የሚጠላውና  የሚጠየፈውና የሚርቀውና አብዝቶ የሚሸሸው ነው ካሶም ደግሞ በጣም የሚወደውነውና አስተውሉ እባካችሁ ለስሜት አትሸነፉ አተኑሩ ስሜታችሁን ተቆጣጠሩ ከክፍ ስራ ራቁ ከማውራት ከማሰብ ከመወሰን ከመተግበር ከመመኘት ከመፈጸም ራቁ ተግታችሁም ጸልዩ

596

## ሰው መግደል በፍቅርስዚም ምህረት የለሽ ሀጥያት ነው

ከፍቅር ስንወጣ በሰውላይ ክፍ ክመመኘት አልፈን መሳደብ መተነኮስ መቅናት ማንካሰስ ማማረር መጥላት ሰውንመምታት መርገም መናቅ አልፈን ስሜታችንን መቆጣጠር አቅቶን  ሰይጣን ገዝቶን ለመጥፎ  ውሳኔ ያበቃናል ከዛ በዋላማ በምድርም የሞት ሞት የስጋትና የጭንቀት ይሆናልና ህይወታችን አምላክ መንፈሱን ከኛ  እርቆ

ሰይጣንም መሞት በምን እድል ያሰኝ ህይወት ያኖረናል ከሞትንም በዋላ ሰይጣን ለ500 አምት ክፍኛ ያሰቃየናልና እናስተውል።

597

ሌሎችም የተከለከሉ በፍቅርሲዚም ውስጥ

- የበዛ ሳቅ ደስታ ጨዋታ ጌም ፊልም መዝናናት ቀልድ ፌዝ ልፊያ አድናቆት የመሳሰሉት ላይ አትዘፈቅ እውቀት የምታገኝበት ከሆነ እንጂ ዝም ብሎ ጊዜህን ለማባከን ብለህ የምታሳልፈው ውሎ ሁሉ ጥሩ አይደለም ካሱምም እየቆየ ይቆጣጠርሃል።
- ወደ አምላክህ አብዙት ትኩረት አለማድረግና ጊዜህን ለፈጣሪ አብዙተህ አለመስጠትህ በማይረባ ግዜያዊ ሱስ ላይ ተጠምደህ መዋል ማደር መክረም፣ መሰንበትና መኖር
- የበዛ እንቅልፍ ና ስንፍና ድካም ሀጥያትን ያመጣል።

598

በውስጥህ ያለው መበሳጨ ት ሲጨምር ተስፋ ስትቆርጥ አምላክን ማመስገን ና መጸለይ ስታቆም የሰው ወሬ አብዝተህ ስትሰማ በበዛ መልክ ራስህን መቆጣጠር ሳችል ስትቀር የመድክም የመስነፍና የመዛል ሁኔታ በህይወትህ ይገጥምሀልና ተስፋየመቁረጥና ደስታና ርካታ የማጣት ሰላም የመራቅ የመሳሰሉት ሁኔታ የሚገጥነምህ በጸሎት እጥረት አማካኝነት ና ለአምላክ ባለህ ትኩረት መቀነስ የሚመጣ ነውና አስተውል።

599

አብዛኛውን ግዜህን ከሰው ጋር ስታወራ ና ስትጫወት ማሳለፍ እግዚአብሄርን ስለምትረሳ ለሱም የምትሰጠው ግዜ አነስተኛና ስለሚሆን አይፈቀድም በዚህም አማካኝነት ከሰው ጋር ስትሆን በማንኛውም መልኩ ቀልብህ አምላክህ ጋር አድርገህ ቆይ በስሜት የሚነዳህ ወሬ ሲፈጠር አምላክህን አስታውስ ወሬውንም በማስቆምም ይሁን በማስቀየር የአምላክህን ከፍያ ውሰድ።

600

ጋብቻ

ወድም ሆነ ሴት ሲጋባ በመጀመር መዋደድና ከምንም ጥቅምና ሌሎች ፍላጎት ላይ ያልተመሰረተ የመውደድ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል እንጂ ሀብትና ንብረት ገንዘብና ዝና አይታ አይቶ ሳይሆን እውቀትና ብቃት እርጋታና ትእግስት ለአምላኩዋ ያላት ታዛዠነት ቅንነትና መልካምነትዋን ያለው ታዛዠ ነት እንጂ ሌላ ማየት አያስፈልግም ከጋብቻ በፊተ ምንም አይነት ግንኙነት መፈጸም አይፈቀድም ቢያንስ ቀለበት ወይንም ማሳወቅ በሽምግልና አለበት ።

ጋብቻውም በጣም ያልተንዛዘና ያልተጋነን በጸሎትና በመዝሙር የታጀበ ቢሆን የፈቀዳል/ይመረጣል።

601

ፍቺ

በፍቅርሲዚም እምነት ፍቺ በፍጹም አይፈቀድም  ሌላ  ቦታ ከማገጡ ብቻ እንጂ ፍቺ  አይፈቀድም ይህን ማድረግ ደግሞ ሀጥያቱ በጣም  የከፋ ነው ከፍቅር አምላክ ቁጣው በጣም ከባድ ነውና ።

ላዚህም ወደ አጥያት እንዳይገቡ በፍቅርሲዝም

አምላክን መፍራት መኖር ይኖርቦታል።

602

ከሚስትህ ጋርለሚኖርህ ግንኙነት  የተከለከለ

አብረሀት እያለ ለስሜት መኖር

ቅጡ የበዛ ግንኙነት መፈጸም

ሌላ ሰው ማሰብና መመልከት ማየት መመኘት መውደድና ማፍቀር ማሰላሰል

ሚስትህን አለመንከባከብና አለመውደድ ና ከአምላክህ በታች  ክብርና ቦታ አለመስጠት

603

ለሚስትህ/ ለባልሽ  ለቤተሰብህ ምንግዜም

መውደድ ና አብረህ መላው ቤተሰብ አምላክህን ማመስግ መጸለይ ለፈጣሪ ሰፊ ግዜ ከቤተሰብህ ጋር መስጠት

ስራ ማገዝ ተጋግዘዞ መስራት ማክበር ከአምላክህ በታች በምትችለው ሁሉ ጊዜ መልካም ባል /ሚስት መሆን

ተስፋና ሰላም መልካም ወሬ ማውራትና አምላክህ ላይ በስፋት መተማመንና ማመስገን  ተግተህ መጸለይ

ለእውነት መወገን ደፋር መሆን ከፈጣሪ ውጪ ማንንም አለመፍራት በመላው ህይወትህ ።

አለመጠራጠር ፣ቅሬታህን ለሰው አለማውራት .በቤትዎቸየተፈጠረቦትን የትኛውንም ችግር መጸለይና ማመን መልካም ተስፋ ማብዛት

ከአምላክህ በታች የተሰጠችህን ሚስትህ/ባልሽ መሆንዋን በማወቅ የሷን ክፍ አታንሳ  ብትሳሳት እንኩዋን  እለፋት ምክንያቱም ይቅርታም አብዛ እሷን ለመቀየም ለመታዘብ ለመጥላት ለማብጠልጠል በልብህ ህሳብ እንዳይገባ አስተውል አምላክን በየትኛውም ሀሳብ ሁሌም አያሰብከው ሁሌም ስለሷ የምታስበው መጥፎ ሀሳብ ካለ አቁም ካለበለዚያ አምላክህን ታጣለህና  እቺ ያገባሀትን ሚስትህን አክብራት እባክህ አስተውል ልብ  በል በየደቂቃው የሚመጣብህን ሀሳብ ሁሉ በየጌዜው አምላክህን እየፈራህ እባክህ ወነድሜ ተህዛዙን አክብር እባክህን /ለአንቺም /ለአንተም/።

604



የምልክቱም ትርጉም  አንድ ብቻ አምላክ ከ1 ውጪ ሌላ አምላክ የለም እስካሁን 151 ነብያቶች ሲመጡም የተጠራው ራሱ 1አምላክ ነው

አምላክ አይታይም አይዳሰስም አይወልድም አይወለድም ሰው አይሆንም ስሜት የለውም አያስብም አያሰላስልም አይደነቅም አይገረምም

የፍቅር አምላክ እግዚአብሄር ሁሉንም ማድረግ ይችላል። ሀያል ነው ታላቅ ነው አዛኝ ነው ይቅር ባይ ነው ሰጪነው አዳኝ ነው  ሁሉን ፈጣሪ ነው ሀሉንም ባንዴ የሚመለከት ነው።

ሁሉን ቻይና በመንፈስ ቀርቦ ይረዳሀል ስህተትህን ይነግርሀል ግን መልካም መሆን ይጠበቅብሀል።

የፍቅር አምላክ ከስሜትና ከአይምሮ በላይነው እኛግን ትንሽ ስለሆንን እናስባለን በስሜቶቻችን ይሰማናል እናዝናለን እንከፋለን አጥያትም እንሰራለን ግንአምላክን ከልባችን ስነፈራ ከአጥያት እንርቃለን ከስሜትና ከክፍሀሳብ እሱን ፈርተን ራሳችንን እንቆጣጠራለን ሃሳብና ስሜታችን  ልባችንን ና መንፈሳችን አንድ  ስናደርግ ከሴጣን እንድናለን መንፈስቅዱስ አንድ ስንሆን ከኛጋር ይሆናል ።

በሀሳብ በስሜት በልቦና በመንፈስ ስንበታትን ማለትም የተለያየ ሀሳብ ቃል /ንግግር/ስሜት/ድርጊት ፍላጎት ሲኖተን መጥፍመንፈስ ይገዛናል ።

የፍቅርአምላክ እግዚአብሄር አንድነው  ከክፍሀሳብና ድርጊት ይጠብቃችሁ።

እዚህ ቅድስ መጽኃፍ ላይ አንተ የተባለውን ለአንቺም ይሆናል አንቺም የተባለው ለአንተም ይሆናል ።

**እዚህ ቅዱስ መጽሀፍ ላይ ያለውን ህግ የማያከብር ኩሳል ሳኮምማ ሳኪር ሁሌም ይጫወትበታል ።**

**ይህ ቅድስ መጹሀፍ ላይ ምንም የጨመረም የቀነሰም የተረገመ ይሁን**

**ይህ ቅድስ ፍቅር መጽሃፍ ገና አላለቀም**

**ይቀጥላል አምላክ ሁሌም በሚሰጠን ተህዛዝም በመንፈስ እስከሚዘጋ ይጻፋል ይቀጥላልም--------**

**የፍቅር አምላክ የሆነ እግዚአብሄር ፡ይግለጽላቹ ፤ይምራችሁ፤ ይባርካችሁም ።**

**አሜን፡**